

# ከሙቀት ጋር የተያያዘ ህመም



## በሙቀት የተነሳ መድከም

**ምልክቶች፡-**

- በከባዱ ማላብ
- ራስ ምታት
- መድከም፣ መዝለፍለፍ፣ ማዞር
- ማቅለሽለሽ ወይም ማስታወክ

***ምን ማድረግ አለብዎት፡-***

- ምልክቶቹ ከአንድ ሰዓት በላይ ከቆዩ ለሐኪም ይደውሉ
- አየር ማቀዝቀዣ ወዳለበት ቦታ ይሂዱ
- ቀዝቃዛ ውሃ ይጠጡ
- ቀዝቃዛ ሻወር ይውሰዱ

## በሙቀት የተነሳ የሚከሰት ስትሮክ

**ምልክቶች፡-**

- በጣም ከፍተኛ የሰውነት ሙቀት
- ግራ መጋባት
- የሚወጋ ራስ ምታት
- ማቅለሽለሽ
- ራስን መሳት

***በሙቀት የተነሳ የሚከሰት ስትሮክ ድንገተኛ አደጋ ነው። አንድ ሰው እነዚህን ምልክቶች ካሳየ ወደ 911 ይደውሉ።***



## ለሞቃት ቀናት በቤት ውስጥ ይዘጋጁ

**የፍጆታ ድንገተኛ አገልግሎቶች ፈንድ (Utility Emergency Services Fund፣ UESF)**
*Front Door Benefits Access Center*
ስለግዛት እና ፌዴራል ጥቅማጥቅሞች ይረዱ እና ይመዝገቡ።
215-814-6845 — BAC@uesfacts.org

*የፍጆታ አገልግሎት እርዳታ ፕሮግራም*
የፍጆታ አገልግሎቶች አደጋ ላይ ከሆኑ ወይም ከተቋረጡ።
215-814-6837 — utility@uesfacts.org

የበለጠ የሙቀት መረጃ በ **phila.gov/heat**።

## ከእኛ ጋር ይገናኙ!

**የማህበረሰብ ምላሽ አጋር አውታረ መረብ**
ከቤተሰብ፣ ከጓደኞች እና ከጎረቤቶች ጋር የሚያጋሩት አስፈላጊ የህዝብ ጤና መረጃ ያግኙ።

bit.ly/CRPNnewsletters




# ሙቀቱን ያሸንፉት!

*በዚህ የበጋ ወቅት Philly ውስጥ ቀዝቀዝ ብሎ ለመቆየት የሚረዱ አስፈላጊ ምክሮች*

Department of Public Health
CITY OF PHILADELPHIA

# አደጋ ላይ ያሉት እነማን ናቸው?

በጣም ሞቃት የአየር ሁኔታ ለሁሉም ሰው አደገኛ ነው።

**አንዳንድ ሰዎች የመታመም ዕድላቸው ከፍተኛ ነው፦**

- 65 ዓመት እና ከዛ በላይ የሆኑ አዋቂዎች
- ጨቅላ ህጻናት እና ትንንሽ ልጆች
- ሥር የሰደደ የጤና እክል ያለባቸው ሰዎች (እንደ የስኳር በሽታ ወይም የልብ ህመም)
- ቤት እጦት ያጋጠማቸው ሰዎች
- ውጭ ወይም አየር ማቀዝቀዣ በሌለበት የሚሰሩ ሰዎች
- አትሌቶች

*ሞቃትና እርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ የአየር ጥራትንም ሊቀንስ ይችላል። እንደ አስም ያለ የመተንፈሻ አካላት ችግር ካለብዎ፣ ከቤት ውጭ የሚያሳልፉትን ጊዜ መገደብ ሊያስፈልግዎ ይችላል።*

**ፊላደልፊያ የአረጋውያን ኮርፖሬሽን (Philadelphia Corporation for Aging፣ PCA) የሙቀት መስመር**

የሙቀት ድንገተኛ አደጋ በሚታወጅበት ጊዜ ከሰለጠኑ ነርሶች የሚሰጡ የሙቀት ደህንነት ምክሮች እና መረጃዎች። ወደ **215-765-9040** ይደውሉ።





# ምን ማድረግ ይችላሉ

**ወቅታዊ መረጃን ያግኙ**

- ከPhilaOEM ነፃ የሙቀትና የአደጋ ማስጠንቀቂያዎችን በቀጥታ ወደ ስልክዎ ያግኙ። ለመመዝገብ **READYPHILA** ብለው በመጻፍ ወደ **888-777** ይላኩ።
- ስለ አካባቢው የአየር ሁኔታ እና የአየር ጥራት መረጃ ያግኙ።

**እንደቀዘቀዙ ይቆዩ**

- የአየር ማቀዝቀዣ ባለበት ቦታ ውስጥ ይቆዩ።
- ቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃንን ያስወግዱ።
- ቀላልና ፈታ ያሉ ልብሶችን ይልበሱ።

**በቂ ውሃ ይጠጡ**

- ብዙ ውሃ፣ የፍራፍሬ ጭማቂ እና ሌሎች ፈሳሾችን ይጠጡ።
- አልኮልን፣ ካፌን እና ስኳር የበዛባቸውን መጠጦች ያስወግዱ።

**የሌሎች ሰዎችን ደህንነት ይከታተሉ**

- ዕድሜያቸው የገፉ አዋቂዎችን እና ከቤት መውጣት የማይችሉ ጎረቤቶችን ይጎብኙ።
- እርዳታ የሚያስፈልገው ቤት የሌለውን ሰው ካዩ፣ ወደ ሚከተለው ቁጥር ይደውሉ **215-232-1984**።

***አንድ ሰው የህክምና ድንገተኛ አደጋ እያጋጠመው እንደሆነ ካሰቡ፣ ወደ 911 ይደውሉ።***

# የከተማ አገልግሎቶች




**የማቀዝቀዣ ማዕከሎች**

በሙቀት ድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ሙቀትን ለመሸሽ እና በአየር ማቀዝቀዣ ለመቆየት የሚረዱ ቦታዎች። በአካባቢዎ የማቀዝቀዣ ማዕከልን ለማግኘት በ**3-1-1** ይደውሉ ወይም bit.ly/PHLHeatSafety ይጎብኙ።



**ስፕሬይ ግራውንድስ (Spray Grounds)**

በዚህ በጋ በውሃ ለመደሰት ነፃ፣ አዝናኝ እና አስተማማኝ መንገድ—እና Philly ከ90 በላይ የሚሆኑት አሏት! በአቅራቢያዎ ያለውን ለማግኘት የሚከተለውን ድህረ-ገጹን ይጎብኙ bit.ly/SpraygroundFinder።



**የህዝብ መዋኛ ገንዳዎች**

መዋኛ ገንዳዎች ሙቀትን ለመቀነስ፣ ለመዝናናት እና ንቁ ለመሆን ጥሩ መንገድ ናቸው።
የመዋኛ ገንዳዎች የሚከፈቱበት ቀናትን ለማየት bit.ly/PublicPoolFinder ይጎብኙ።



**የመጫወቻ ጎዳናዎች**

በየሳምንቱ የስራ ቀን በበጋ ወቅት መንገድዎ ተዘግቶ ለህፃናት ነፃ ምግብ ለማቅረብ እና ከቤት ውጭ እንዲጫወቱ ያስችላቸዋል።
የመጫወቻ ጎዳና ለመሆን ያመልክቱ! በ **215-685-2719** ይደውሉ ወይም **bit.ly/PHLPlaystreets** ይጎብኙ።